# ሠ ቅ ዷ ሌ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!



ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም ፳ | ጥር ፲፱ ፪ሺ፲

በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## ፍትሕ ለዐማራ ሕዝብ!

ኢትዮጵያ አገራችን በዘመኗ ሁሉ ብዙ ፈተናዎችን አሳልፋለች።አሁን የገጠማት በዓይነቱም ሆነ በብዛቱ በወርዱም ሆነ በቁመቱ ዘመናት ከደቀኑባት ሁሉ የተለየ ነው።ከዚህ ውስጥ አንዱ ሕዝቦቿ ጎራ ለይተው በጎጥ ተቧድነው፣ ዘረኞች እር በርሳቸው እንዲፋጁ የደገሱላት የመጠፋፋት ድግሥ ነው። ለዚህ ዕኩይ ግባቸው የመስዋዕት ጠቦት ያደረጉት ደግሞ ዐማራውን ነው። ወደ ተሻለና የሁሉም ዕኩልነት የተረጋገጠባት ዴሞክራሲያዊት አገር እንደመመሥረት እና ሁኔታዎችም ይህንኑ ፈቅደውላቸው እያለ ወደ ኋላ ቀር የዘርና መንደር ናፋቂነት የወሰዱን ዘረኞች፣ በሕዝባችን ላይ የፈጸሙትን የግፍ ዓይነት ዘርዝሮ ለመግለጽ አዳጋች ነው። ይህንን ኢሰብአዊ ወንጀል ለመፋረድና ፍትሕ ለሁሉም በዕኩል እንዲደርስ ወንጀለኞችን በፍትህ አደባባይ ለመፋረድ  ሕዝቡ ሙሉ ዝግጅቱነቱን በአደባባይ እየገለጠ ነው።

ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ዘመንና ወቅትን እየጠበቁ ጊዜያዊ ጉልበት ያገኙ፣ ጉልበት አልባዎችን እንዳይበቀሉ እና ይህ ዕውደት እንዳይቀጥል የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት እንዳለበት የምዕላተ-ሕዝቡ አቋም እየሆነ ነው። ሁሉም በእቅሙ ሳይታበይ በፍትሕ እንዲዳኝ፣ የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ሞትና ግድያ ያለእዳቸው በማንነታቸው ብቻ በተጨፈጨፉት ዐማራ እህቶቻችንና  ወንድሞቻችን ያብቃ፤ ለዚህም ወንጀለኞች በሕግ አደባባይ ይዳኙ፤ የሚሉ ድምፆች አድማስ አድማስ እያስተጋቡ ነው። «ዓይን ያጠፋ፣ ዓይኑ ይጥፋ» የሚለው ብሂል ፣ወደ በቀልና ወደ እማያቋርጥ ተካታታይ የእልቂት አዙሪት ስለሚከት፣ ለሕዝባችንም የጋራ መፃዒ ዕድል አዎንታዊ ጎሕ ስለማይቀድ፣ከመጠፋፋቱ አዟሪት ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መውጣት ይኖርብናል። ይህን ዘመኑ የሚዋጀውን የሰለጠነ መንገድ በመከተል የተበደሉና የተገፉ ወገኖች ፍትህና ርትዕ ሊያገኙ የሚችሉበትን የአሠራር ጎዳና መከተል ተገቢ እንደሚሆን  ድርጅታችን  የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት በጽኑ ያምናል።

# ፍትሕ ለዐማራ ሕዝብ!

ለሰው ልጅ ከሕይዎቱ የበለጠ ውድ ነገር ከቶ ምን አለ? በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዐማሮች ያለዕዳቸው በኢትዮጵያ ምድር ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ተጨፍጭፈዋል።ከሁሉም የማይዘነጋው ከሞታቸው ያሟሟታቸው ሁኔታ ነው። ናዚዎች በይሁዳውያን ላይ ከፈጸሙት የበለጠ ግፍ የተፈጸመባቸው ሲሆን፣ በሰው ልጅ አመክንዮ ሲፈተሽ፣ ደምን ለመመለስ ከመዘጋጀት ውጭ ሌላ መፍትሔ ለመሻት አይዳዳም። ሆኖም፣ ደምን በደም ቢያጥቡት ተመልሶ ደም ነውና፣ የኋላ ቀሮችን ኮቴ ተከትሎ መንጎዱ፣ ዘላቂ ሰላምና መረጋጋትን ለአገራችን ያስገኛል ተብሎ አይታሰብም። ከመጠፋፋት ወጥተን፣ ሕዝባችን በሰውነቱ በሕግ ፊት ዕኩልነቱ ተረጋግጦ፣ ሁሉም ዕኩል ፍትሕ የሚያገኙበት ሥርዓት መዘርጋት ለአንድነታችንም ሆነ ለተፋጠነ ዕድገታችን ዋስታና እንደሆነ ይታመናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ፣ ዕኩልነት፣ ዴሞክራሲና የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን የሚጥሩ ሁሉ፣ ጥረታቸው የሰመረ የሚሆነው ለፍትሕ ያላቸው አቋምና እምነት የማይናወጥ ሲሆን ነው ብለን እናምናለን። ይህ፣ የእኛ የዐማሮች ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የሁሉም አገሬን እወዳለሁ የሚል ኢትዮጵያዊ ሁሉ እምነትና በወል ወደ ተግባር የሚለወጥ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው።ለጥቃቅን ጊዜአዊ ጥቅሞችና ለቡድን ፍላጎቶች ተከፋፍለን ባንቆም ኖሮ፣ የትግሬ-ወያኔ ዛሬ በአገራችንና በወገናችን ላይ ያደረሰው ሁለንተናዊ ጥፋት አይደርስም ነበር። «ዐማሮች ወንድሞቻችንን አትግደሉ ፣አታፈናቅሉ፤ የእነሱ ሞትና መፈናቀል የእኛም ነው።» ብለን በጋራ ብንቆም ኖሮ በየተራ ለተፈጸሙብን ግፋና መከራ ተጋላጭ አንሆንም ነበር። በአገራችን ረጅም ታሪክ አብረው ከመኖር አልፈው በሥጋ ልደት የተዋሐዱ  የሌሎች ነገዶች አባሎች ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የእኛ የዐማራው ተጥሎ መጠቃት የነርሱም መጠቃት መሆኑን ማወቅ ነበረባቸው። ይህ ቢሆን  ኖሮ፣ ጭርሱንም በዐማራነትም መደራጀት ባላስፈለገን ነበር። ምክንያቱም  ጥቃቱ የሁላችንም በመሆኑ፣ ጥቃቱን በጋራ እንመክት ነበር እንጂ፣ በዐማራነት ከመንጋችን ተለይተን ስለዐማራ አንጮሕም ነበር። ይህ ባለመሆኑ ግን፣  ኀልውናችን ለማስቀጠል ስንል፣ በዐማራነት መደራጀት ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ሆኖ፣ በመቅረቡ ተደራጅተን የሌሎችን ኢትዮጵያውያንን አንድነትና ኅብረት አስፈላጊነት  መስበኩን ሥራችን አድርገን ይዘነዋል።

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዐማሮች አገር ሰላም ብለው በሚኖሩበት አገር ኢ-ሰብአዊ ፍጅት ተፈጽሞባቸዋል። ይህ ግምት ወይም አሉባልታ አይደለም። የተጨበጠ አኃዛዊ ጥናታዊ መረጃ በጃችን አለ። የሰው እማኝ ፤ የሰነድ ማረጋገጫ ፤ የድምጽ ማስረጃ ወዘተ ተመዝብጎና ተቀርጾ ባግባቡ በፍትሕ አደባባይ ለመቆም ቀኑን በመጠባበቅ ላይ ነው።

ማንም በግልጽ እንደሚረዳው፣ በዐማራው ነገድ ላይ የተፈጸመው ጭፍጨፋ በራሱ የሆነ፣ ወይም የተፈጥሮ አደጋ ያመጣው ሳይሆን፣ «የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር» በተለምዶ ወያኑ በሚል መጠሪያ የተደራጁ ሰዎች፣ እንዲሁም  እራሱን ኦነግ ብሎ ከሚጠራው ድርጅት ጋር በመቀናጀት በትዕዛዝና በመዋቅር ሆን ብለው የፈጸሙት፣ በኢትዮጵያ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ  በአንድ ዘር ላይ የተፈጸመ ወንጀል ነው። ስለሆነም፣ ይህን ወንጀል እንዲፈጸም  መመሪያ ያዘጋጁ፣ያዘዙ፣ ያስፈጸሙ እና ያስፈጸሙ ሁሉ በፍትሕ አደባባይ ፍርዳቸውን እንዲያገኙ ማድረግ ለፍትሕ ቆመናል የሚሉ ወገኖች ሁሉ የጋራ ጥረት ሊሆን ይገባል እንላለን። ለኢትዮጵያ አንድነት፤ ለሕዝቡ ነፃነት፣ ዕኩልነት፣ ማኅበራዊ ሰላም መረጋገጥና ለጋራ ብልጽግና መሠረቱ የፍትሕ ሥርዓቱ በአስተማማኝ ሁኔታ መዘርጋት ነው።

# ፍትሕ ለህማሩ ሕዝብ!

የዚህ ተጫባጭ ማሳያውም ፣በኢትዮጵያውያን ላይ የዘር ማጥፋትና የዘር ማጽዳት ወንጀል በፈጸሙ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ ወደ ፍትሕ እንዲቀርቡ በሚደረገው ጥረት ይገለጣል።

በዚህ ጉዳይ ዞሪያ ሰብአዊነት የሚሰማቸው ነግ በኔን የሚያውቁ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሊረባረቡበት እንደሚገባ እናምናለን። ይህ ካልሆነና ዘረኞች ከሥልጣን ማማ ላይ እስካልረገፉ ድረስ፣ የዘር ጥፋት አዙሪት እንዲሁም መፈናቀል ለሁሉም እንደማይደርስ ምንም ዋስትና የለም። ለዚህም በቅርቡ በሶማሌንና በኦሮሞን ነገዶች መካከል አገዛዙ ሆን ብሎ አቅዶና አልሞ የመራው ዘር ተኮር ግጭትና ማፈናቀል ዋና ማሳያ ነው።

አንድ ሕዝብ መርጦ ባልተወለደበት ተፈጥሮአዊ ሁኔታ፣ ዘሩ እየተለየ ሲመነጠርና ኅልውናው አደጋ ላይ ሲወድቅ ከማንም ቀድሞ ጥቃቱን መከላከል ያለበት ራሱ ነው። ***«ባለቤት ካልጮኸ ጎረቤት አይደርስም»*** የሚባለው የአባቶቻችን ብሂል ጎልቶ ማስተጋቢያው አንዱ አጋጣሚ ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ነው። ዐማራው ወያኔ ከደደቢት በርሃ ትግሉን ሲጀምር፣ «አውራ ጠላቴ ዐማራ ነው፣ ዐማራ ካልጠፋ ፣የትግራይ ሕዝብ ማኅበራዊ ሰላም አያገኝም» ብሎ አቅዶ ሲንቀሳቀስ፣ ዐማራው ከተደገሠለት የጥፋት ድግሥ ራሱን ለመከላከል የሚያስችሉ ዝግቶችን ለማድረግ በተለያዩ ምክንያቶች ማድረግ አለመቻሉ፣ አሁን ለደረሰው የዘር ጥቃት ተጋላጭ እንዲሆን እንዳደረገው ነባራዊ ሁኔታው ያሳያል። ከጥፋቱ ድግሥ ራሱን ለመጠበቅ ፈጥኖ መደራጀት አለማቻሉ፣ ሁኔታዎችን በማቅማማት መመልከቱ፣ ወያኔን እንደመንግሥት መቁጠሩ፣ ራሱን ከጥፋት ለመከላከል መሞከርን ወያኔአዊ ድርጊት አድርጎ መቁጠሩ፣ በነገዱ ላይ እየተፈጸመ ያለውን የዘር ዕልቂት አቅሎ መመልከቱ፣ የገጠመውን ገሃዳዊ ፍልሚያ እንዳላየ በማየት ሆድ ይፍጀው እያለ በትዕግሥት መመልከቱ፣ ወዘተ በነገዱ ላይ የተፈጸመውን ግፍ እንዲበራከት አድርጓል። ይህ ይሁን እንጂ፣ ለሁሉም ጊዜ አለውና፣ በነገዱ ላይ እየተፈጸm ያለው ግፍና መከራ ማቆም አለበት ብለው የተነሱ ወገኖች፣ ዐማራው ከድል መልስ ወደኋላ ሊመለስ ከማይችልበት የፍልሚያ ሜዳ ውስጥ ከተውታል። ዐማራው እራሱን ለማዳን በወቅቱ አለመነሳቱ ለዘረኞች ግፍ ተጠናክሮ መቀጠል አጋዥ ከመሆን አልፎ፣ ዐማራውን አስንቆታል። ይህም ለዐማራው ወጣት ትውልድ የእልህ ሥንቅ በመሆን ራሱን አደራጅቶች፣ ከመሰል ወገኖች ጋር ወያኔን ለመታገል ቁርጥ ውሣኔ አድርጎ፣ የወያኔን የሥልጣን ማማ እያመዛወዘው ይገኛል።

ዐማራ ነኝ የምትል ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣ አያት ቅድመአያቶችህ፣ ለአንድነቷና ለሉዓላዊነቷ መጠበቅና መረጋገጥ አጥንታቸውን የከሰከሱላት፣ ደማቸውን ያፈሰሰሱላት አገርህ ብቻ ሳትሆን፣ የማንነትህና የኅልውናህ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ደርሷልና እጅ ለእጅ ተያይዘህ ተነስ። አደጋው በግልጽ የገባን ዐማሮች በውጭም ሆነ በአገር ውስጥ ተደራጅተን የአናሳ ዘረኞችን አገዛዝ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ መንጭቆ ለመጣል ፍልሚያ ላይ ነንና ተቀላቀለን። ከሁሉም በላይ ያለጥፋታቸው ገደል የተጣሉት፤ ጡታቸው የተቆረጠው ፤ በገጀራ እንደ እንስሳ የተቆራረጡት ፤ ከእናቶቻቸው አንቀልባ ተመንጭቀው ወደ እቶን እሳት የተጣሉት ጨቅላ ሕፃናት ፤ ለዘመናት ከኖሩበት ቀዬ የተፋነቀሉት በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ዐማሮች ደም ይጮሃልና ልትፋረድ የምትችለው አንተ በሕይዎት ያለህ ዐማራ ብቻ ነህና ሳታወላውል ትግሉን ተቀላቀል!

የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስታ ነው!